የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፩ አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 41 ADDIS ABABA, 7th May, 2025

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፯
የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ…………………………ገጽ ፲፰ሺ፫፻፶፮

**Content**

Regulaton No. 1/2024
Federal Courts Court Fee Regulation ………..………………......Page 18356

## ደንብ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፯
## የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የፌደራል ፍርድ ቤቶች እስከ አሁን ድረስ የሚጠቀሙበት የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የህግ ክፍል ማስታወቂያ ደንብ በ፩ሺ፱፻፵፭ ዓ.ም የወጣ እና ማሻሻያ ሳይደረግበት የቆየ በመሆኑ እና በደንቡ ያልተሸፈኑ በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው ወቅቱን እና ጊዜውን የዋጀ የዳኝነት ክፍያን መወሰኛ ደንብ በማስፈለጉ፤

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አሁን ከደረሱበት ወቅታዊ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ እና ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት ክፍያ ማስከፈል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዳኝነት አከፋፈል ሥርአቱን ለማዘመን እና የክፍያ ሥርአቱን አጭር፤ ቀልጣፋ እና ለከፋዩም ያመች ዘንድ ከጊዜው ጋር የተሻሻለ የዳኝነት አከፋፈል ሥርአት እንድኖር ለማስቻል ይህንን ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፕሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፪ሺ፲፫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## REGULATON NO 1/2024
## FEDERAL COURTS COURT FEE REGULATION

**WHEREAS,** the Court Fee Rule of 1952, has remained enforceable in Federal Courts until now without any amendments, despite the fact that various issues are not covered by this rule and there is a need for the determination of a court fee Regulation that takes in to account the current situation and time;

**WHEREAS,** it is deemed necessary to charge a court fee commensurate with the current standard of judicial service delivered by the Federal Courts;

**WHEREAS,** it is deemed necessary to enact this regulation in order to modernize the court fee payment system and make it shorter, more efficient, and more convenient for the payer;

**NOW, THEREFORE,** the House of Peoples' Representatives Proclaimed the Federal Courts Court Fee Regulation in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Federal Courts Proclamation No. 1234/2021 as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የዳኝነት ክፍያ ደንብ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፯ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"።

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩/ "**አዋጅ**" ማለት የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፪ሺ፲፫ ማለት ነው፡፡

፪/ "**ፍርድ ቤቶች**" ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

፫/ "**ሬጅስትራር**" ማለት በሌላ ሕግ የተሰጠው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ሹመት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፬/ "**በገንዘብ የሚተመን ክስ**" ማለት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ ገንዘብን የሚመለከት ወይም ክስ የቀረበበት ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ማናቸውም ንብረት በገንዘብ ሊተመን የሚችል ማለት ነው፡፡

፭/ "**በገንዘብ ሊተመን የማይችል ክስ**" ማለት በባህሪያቸው በገንዘብ ሊገመቱ የማይችሉ ወይም ከግለሰብ ስብዕና ጋር የተያያዙ የመብት ማስከበር አቤቱታዎች ማለት ነው፡፡

፮/ "**አቤቱታ**" ማለት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ለፍርድ ቤት የቀረበ ክስ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት፣ የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ፣ የሰበር ማመልከቻ፣ ድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ እና ማናቸውም ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ማለት ነው፡፡

፯/ "**የዳኝነት ክፍያ**" ማለት ክስ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ፣ የይግባኝ አቤቱታ፣ መስቀለኛ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ መቃወሚያ ወይም የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ወገን እንደዚሁም በዚህ ደንብ መሰረት ሊከፈሉ የሚገቡ ማናቸውንም ክፍያዎች የሚመለከት ነው፡፡

## SECTION ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as "Court Fee Regulation No. 1/2024".

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context requires otherwise;

1/ **"Proclamation"** shall mean the Federal Courts Proclamation No. 1234/2021.

2/ **"Federal Courts"** shall mean Federal Supreme Court, Federal High Court and Federal First Instance Court.

3/ **"Registrar"** shall mean, without prejudice of responsibilities vested in him by other laws, the person appointed by the Federal Judicial Administration Council in accordance with the appropriate law,

4/ **"Monetary claims"** shall mean any case involved with a specified amount of money or any movable or immovable property whose value can be estimated in terms of money.

5/ **"Non-monetary claims"** shall mean claims, in their nature, attributable to the enforcement of the personal rights of a human person and cannot be estimated in terms of money.

6/ **"Pleading"** shall mean a statement of claim, Counter-claim, an application for intervention, an application for Cassation, an application for Review of judgment and any other application filed in the court in accordance with the appropriate law.

7/ **"Court Fee"** shall mean a fee to be paid by the party that filed a statement of claim, Counter-claim, a memorandum of appeal, cross appeal, cross objection or an application for Cassation or any fee to be paid in accordance with this Regulation.

፰/ **"ግምት"** ማለት በዚህ ደንብ በተቀመጠው ታሪፍ መሰረት አንድ የዳኝነት አገልግሎት ለተጠየቀበት ጉዳይ የሚያስፈልገው የክፍያ መጠን ማለት ነው።

፱/ **"ደሀ"** ማለት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዳኝነት ክፍያ መክፍል የማይችል ሰው ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፩ እስከ ፭) መሰረት በድሃ ደንብ እንዲከራከር የተፈቀደለት ሰው ማለት ነው፡፡

፲/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፲፩/ በዚህ ደንብ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴት ፆታንም ያጠቃልላል፡፡

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ ደንብ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፪/ ይህ ደንብ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ የፌደራል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡

፫/ የክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና ሥልጣን በሚመለከቷቸው የፌደራል ጉዳዮች ላይ ደንቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፬. <u>ዓላማ</u>

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መሰረታዊ መብትን በማይጋፋ መልኩ ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት ክፍያ እንዲያስከፍሉ ማስቻል፤

፪/ የዳኝነት ክፍያን በማሻሻል ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በመስጠት የዳኝነት አገልግሎትን ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፤

፫/ የዳኝነት ሥርዓቱ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆን፣ አንዳንድ የክስ ምክንያት የሌላቸው ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ በማድረግ ለዳኝነት ሥራ አካሄድ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻል።

8/ "**Estimate**" shall mean the amount of fee to be paid for the Judicial service in accordance with the tariff stated in this Regulation.

9/ **"Pauper"** shall mean a person who cannot pay the prescribed court fee in accordance with the appropriate law or a person who is given a leave to sue as a pauper in accordance with Article 21 Sub articles (1-5) of this Regulation.

10/ **"Person"** shall mean Natural or Juridical person.

11/ Any expression in the masculine gender shall also include the feminine gender.

## 3. <u>Scope of Application</u>

1/ This Regulation shall be applicable on any suit instituted in the Federal Courts.

2/ This Regulation shall be applicable on any Suit in relation to Federal matters instituted in the Addis Ababa and Diredawa City Courts.

3/ The Regulation shall be applicable on Federal Matters adjudicated by state Courts in their Concurrent Jurisdiction.

## 4. <u>Objective</u>

This Regulation shall have the following Objectives:

1/ Enables Federal Courts to charge reasonable court fees for services rendered in a manner that does not infringe on Citizens Fundamental Rights to Access to Justice;

2/ Enables the Judicial Service to be more effective by improving Court Fee which helps to provide modern and efficient Judicial Services to Society;

3/ To make the judicial system accessible to citizens, prevent some groundless cases from being brought before the court, and create a favorable environment for the judicial service process.

## ክፍል ሁለት
## የዳኝነት ክፍያ አከፋፈል

**፭. የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ ስለሚከፈልበት ጊዜና የአከፋፈል ሥርዓት**

፩/ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት ከዳኝነት ክፍያ ነፃ ካልተደረገ በስተቀር ማንኛውም አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ያቀረበ ወገን የዳኝነት ክፍያ መክፈል አለበት።

፪/ በደሀ ደንብ እንዲከራከር ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር በየደረጃው የሚገኙ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሬጅስትራሮች አቤቱታ የሚያቀርበዉን ማንኛዉንም ወገን የዳኝነት ክፍያ የማስከፈል ኃላፊነት አለባቸው።

፫/ የዳኝነት ክፍያ የሚፈጸመው ፍርድ ቤቱ አመቺ ነው ብሎ ባመነበት በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ በኩል፣ በክሬዲት፣ በዴቢት ካርድ ወይንም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ሊሆን ይችላል፡፡

፬/ የዳኝነት ክፍያ የሚፈጸመው የፍርድ ቤት መዝገብ ከመከፈቱና ቁጥር ከመሰጠቱ በፊት ነው፡፡

፭/ የሚመለከተው የፍርድ ቤት ሰራተኛ ወይም ሬጅስትራር በዚህ ደንብ መሰረት የዳኝነት ክፍያ መከፈሉን ሳያረጋግጥ የፍርድ ቤት መዝገብ መክፈት ወይም እንዲከፈት ማድረግ የለበትም።

፮/ ባለጉዳዮች በኢ-ፋይሊንግ ሥርዓት፣ በድረ-ገጽ ወይም በኢንተርኔት በመጠቀም አቤቱታ ማቅረብ በሚችሉበት ወቅት ክፍያውን በክሬዲት ካርድ፣ በዴቢት ካርድ፣ በኤልክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ወይም አመቺ በሆኑ ሌሎች የክፍያ ዘዴዎች አማካይነት መፈጸም ይችላሉ፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በየደረጃው የሚገኙ ሬጅስትራሮች የዳኝነት የአገልግሎት ክፍያን ሲያስከፍሉ፣ ክስ የቀረበበት ጉዳይ በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን አለመሆኑን እና ሊከፈል የሚገባውን መጠን በጥንቃቄ በመለየት ክፍያው እንዲፈጸም ለሚመለከተው ሰራተኛ ወዲያውኑ ማስተላለፍ አለባቸው፡፡

፰/ አቤቱታ አቅራቢው የዳኝነት ክፍያውን በአግባቡ መክፈሉ ሲረጋገጥ እንደክፍያው ዘዴ አይነት ተገቢው የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም አጭር የኤሌክትሮኒክስ መልዕክት እንዲደርሰው ይደረጋል።

## SECTION TWO
## PAYMENT OF COURT FEE

**5. Time and System of Payment of Court fee**

1/ Unless otherwise exempted by this Regulation and other Laws, any party who file a Suit with the Court shall pay the court fee.

2/ Except for a Person permitted to litigate as a pauper, Registrars at all levels of Federal Courts are responsible for charging a court fee any party filing a Suit.

3/ Court fee may be paid by cash, bank, credit card, debit card or electronic payment method as the court deems convenient.

4/ The court fee shall be paid before the Suit File is opened and Numbered.

5/ The authorized court officer or registrar shall not open or cause to be opened the file without verifying the Payment of the Court Fee is in accordance with this Regulation.

6/ When parties can file the suit using the e-filing system, website or internet, the payment may be made through credit card, debit card, electronic payment method or other convenient payment method.

7/ When registrars at all levels cause the court fee to be paid in accordance with Sub Article (1) of this Article, they must carefully examine whether the case involves monetary claims or not and the amount to be paid, and immediately transfer it to the authorized officer to make the payment.

8/ When it is confirmed that an applicant has paid the required court fee properly, he shall receive an appropriate payment confirmation document or a short electronic text message depending on the types of payment methods.

፱/ መዝገብ ተከፍቶ የቀረበለት ችሎት በዚህ ደንብ መሰረት መከፈል የሚገባው የዳኝነት ክፍያ መከፈሉን ማረጋገጥ አለበት።

**፮. የዳኝነት ክፍያ መጠን አወሳሰን**

የዳኝነት ክፍያ መጠን የሚወሰነው በዚህ ደንብ ላይ በተመለከተው አግባብ የቀረበውን አቤቱታ በመመልከት ደንቡን መሰረት በማድረግ በሚገኝ ተመን ላይ ተመስርቶ ነው።

**፯. በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች**

ለፍርድ ቤት የቀረበው አቤቱታ በገንዘብ ሊተመን የሚችልን ጉዳይ የሚመለከት ከሆነ በጉዳዩ የገንዘብ መጠን ላይ በመመስረት በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው የዳኝነት ክፍያ ተመን ሠንጠረዥ ላይ በተመለከተው አግባብ በመቶኛ ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያው መከፈል አለበት።

**፰. በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች**

በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች መሰረት በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ የተለያዩ አቤቱታዎች ለፍርድ ቤት ሲቀርቡ በሚከተለው መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይፈጸማል፡-

፩/ አቤቱታው የቀረበው ለፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

፪/ አቤቱታው የቀረበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፩ሺ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

፫/ አቤቱታው የቀረበው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

፬/ በቤተሰብ ሕግ መሰረት በባልና ሚስት መካከል ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግን ውል በፍርድ ቤት ለማረጋገጥ ለሚቀርብ አቤቱታ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

፭/ ጊዜው ያለፈበት የይግባኝ ወይም የሰበር ማስፈቀጃ አቤቱታ ለማቀርብ ብር ፩፻ (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

9/ The bench to which the file is referred must ensure the payment of required court fee to be paid as per this Regulation.

**6. Determination of the Amount of the Court Fee**

The amount of the court fee shall be determined based on the rate stated in this Regulation after reviewing the filed applications.

**7. Suits with Monetary Values**

If the application filed to the court relates to a matter that can be estimated in monetary values, taking into account amount of money involved in the case, the court fee should be calculated based on the percentage stated in table attached to this Regulation.

**8. Non-Monetary Claims**

When various non-monetary claims are brought to the court according to the Civil Procedure Code, the Federal Courts Proclamation or other laws, the court fee shall be paid as follows;

1/ If the application is submitted to the Federal First Instance Court, Birr 1,000 (One Thousand) shall be paid as follows:

2/ If the application is submitted to the Federal High Court, birr 1,500 (One Thousand Five Hundred) shall be paid.

3/ If the application is submitted to the Federal Supreme Court, Birr 2,000 (Two Thousand) shall be paid.

4/ 500 (Five Hundred) birr shall be paid for an application brought to the Court for the approval of a Contract made between spouses regarding their property according to the Family Code.

5/ Birr 100 (One Hundred) shall be paid to submit an application for leave to Appeal or Cassation out of time.

፮/ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ በሚታይ ጉዳይ ጊዜአዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ፣ የግልግል ዳኝነት በፍርድ ቤት አማካይነት እንዲሾም፣ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም ሌላ ትዕዛዝ ተፈጻሚ እንዲሆን ለሚቀርብ ማናቸውም አቤቱታ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

## ፱. ተጣምረው ስለሚቀርቡ የክስ ምክንያቶች

በአቤቱታ አቅራቢው ከአንድ በላይ የክስ ምክንያቶችን በአንድ ላይ አጣምሮ በሚያቀርብበት ጊዜ ለእያንዳንዱ የክስ ምክንያት አግባብነት ባለው የዚህ ደንብ ድንጋጌ መሰረት ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል።

## ፲. ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈሉ ክፍያዎች

፩/ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ከተደረጉ ወገኖች በስተቀር በፍርድ ቤት ለሚሰጡ ማናቸውም አገልግሎቶች ክፍያ መፈጸም አለበት።

፪/ ከዚህ በታች ለተመለከቱት አገልግሎቶች የሚከፈለው ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ለተከራካሪ ወገን ወይም ለምስክር መጥሪያ ለማውጣት ለእያንዳንዱ ምስክር ብር ፶ (ሃምሳ ብር) ይከፈላል፤

ለ) የፍርድ ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውንም የሰነድ ወይም የኤሌክትሮኒክ ሰነድ በፍርድ ቤቱ ኮፒ ተደርጎ የሚሰጠው ከሆነ በገጽ ብር ፭ (አምስት ብር) ይከፈላል፤

ሐ) ከላይ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ውጪ ከፍርድ ቤቱ ከተጠየቀ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ጋር ተመሳሳይ በሆነ ርዕስ ሥር የተመለከተው ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል።

## ፲፩. በክለሳ ወይም በይግባኝ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

በሕግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት በተለያዩ የአስተዳደር ተቋማት ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች በፍርድ ቤት በይግባኝ ወይም ቀጥታ ክስ ለሚቀርብ አቤቱታ ከዚህ በታች የተመለከተው ክፍያ ይከፈላል፡፡

፩/ አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

6/ Birr 2,000 (Two Thousand) shall be paid for an application of requesting the grant of a temporary provisional measure or injunction order, for the appointment of an arbitrator by the Court and an application to enforce a temporary provisional measure or any order given by arbitrator.

## 9. Joinder of Causes of Action

When the applicant files more than one cause of action jointly, the Court Fee shall be calculated and paid for each cause of action in accordance with the relevant Provisions of this Regulation.

## 10. Fees for Various Services

1/ Fees shall be paid for any service provided by the Court, except for parties exempted from court fees by this Regulation or by other laws.

2/ The Fees for the services mentioned below shall be as follows:

A) 50 (Fifty Birr) shall be paid for each witness to issue a summons to a disputing party or a witness.

B) For taking a copy of a decision or any document or electronic document found in the file, a fee of 5 (Five Birr) shall be paid per page if the copy is to be made by the court.

C) If services other than those mentioned above are requested from the court, the Court shall order the Payment under the same headings as the services mentioned above.

## 11. Court Fees for Review and Appeal Cases

For cases adjudicated by various administrative institutions in accordance with the power given to them by law and brought to the court directly or on Appeal, the amount of the Fees shall be as

1/ Birr 1,000 (One Thousand) shall be paid if the appeal is lodged to the Federal First Instance Court.

፪/ አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

፫/ አቤቱታው በይግባኝ የቀረበው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበ ከሆነ ብር ፫ሺ (ሶስት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

፬/ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

፭/ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

፮/ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የቀረበው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር ፩ሺ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

**፲፪. <u>በክርክር ሂደት ወይም ከውሳኔ በኋላ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ስለሚከፈል ዳኝነት</u>**

አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወይም በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት በቀረበ አቤቱታ ለሚሰጥ አገልግሎት ቀጥሎ የተመለከተው የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡-

፩/ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ውሳኔ አስነስቶ ወደ ክርክሩ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ ብር ፭፻ (አምስት መቶ) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፪/ ፍርድን ለመቃወም ለሚቀርብ አቤቱታ መቃወሚያውን ያቀረበው ወገን አስቀድሞ ተከፍሎ በነበረው ክፍያ ልክ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል።

፫/ በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ አመልካቹ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል።

2/ Birr 2,000 (Two Thousand) shall be paid if the appeal is lodged to the Federal High Court.

3/ Birr 3,000 (Three Thousand) shall be paid if the appeal is lodged to the Federal Supreme Court.

4/ Birr 500 (Five Hundred) shall be paid, if the application is for the review of the decision given by the Administrative Agency is submitted to the Federal First Instance Court.

5/ Birr 1,000 (One Thousand) shall be paid, if the application is for the review of the decision given by the Administrative Agency is submitted to the Federal High Court.

6/ Birr 1,500 (One Thousand Five Hundred) shall be paid, if the application is for the review of the decision given by the Administrative Agency is submitted to the Federal Supreme Court.

**12. <u>Court Fees to be Paid for Applications During or After Litigation</u>**

When the application is brought to the Court after a judgment, decision or order is given, or during or after the Court to which the application is filed renders a Judgment, decision or order in the case, or for service rendered for a petition to intervene in the litigation process, the following Court Fee shall be paid:

1/ Birr 500 (Five Hundred) shall be paid for an application to be a party in the litigation by setting aside of the Decision rendered ex-parte.

2/ A party who brings an application to oppose the judgment shall pay Court Fee in similar extent to the already paid amount.

3/ An applicant who brings an application for intervention into a litigation, without taking into account the Amount of the dispute, shall pay Birr 1,000 (One Thousand) court fee.

## ፲፫. አቤቱታ ሲሻሻል ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

ከተከራካሪ ወገኖች አንዳቸው በክርክር ሂደት ውስጥ የአቤቱታ ማሻሻል ጥያቄን ጨምሮ በሚያቀርቡት ማመልከቻ ምክንያት የክርክር ሂደቱ ወደኋላ የሚመለስ ከሆነ ክርክሩ የደረሰበትን ደረጃ፣ የፍርድ ቤቱን ጊዜ እና ወጪ ከግምት ውስጥ በማስገባት አቤቱታ አቅራቢው መጀመሪያ በቀረበው ክስ ላይ ተከፍሎ የነበረውን የዳኝነት ክፍያ ፲ ከመቶ (አስር ከመቶ) የማይበልጥ እንዲከፍል ችሎቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፬. ፍርድ ለማስፈጸም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ

ፍርድ ከተፈረደ በኋላ ፍርድ ለማስፈፀም ለሚቀርብ የአፈጻጸም ማመልከቻ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይፈጸማል፡-

ሀ) ፍርድ ያረፈው ከዜሮ እስከ ብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር ፫፻ (ሶስት መቶ ብር) ይከፈላል፤

ለ) ፍርድ ያረፈው ከብር ፩፻ሺ.፩ (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፤

ሐ) ፍርድ ያረፈው ከብር ፪፻ሺ.፩ (ሁለት መቶ ሺህ አንድ ብር) አስከ ፭፻ሺ (አምስት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ይከፈላል፤

መ) ፍርድ ያረፈው ከብር ፭፻ሺ.፩(አምስት መቶ ሺህ አንድ ብር) አስከ ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) ከሆነ ብር ፩ሺ.፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) የዳኝነት ይከፈላል፤

ሠ) ፍርድ ያረፈው ከብር ፩ ሚሊዮን ፩ ( አንድ ሚሊዮን አንድ ብር ) እስከ ብር ፲ ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን ብር) ብር ከሆነ ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር) የዳኝነት ይከፈላል፤

ረ) ፍርድ ያረፈው ከብር ፲ ሚሊዮን ፩ (አሥር ሚሊዮን አንድ ብር) በላይ ከሆነ ብር ፫ሺ (ሶስት ሺህ ብር) የዳኝነት ይከፈላል፤

## 13. Court Fee for the Amendment of a Pleading

If one of the parties in the case requests for the amendment of the pleading and that will cause delay the proceedings, the court may order the applicant to pay not more than 10 (ten) percent of the already paid court fee, and this will be determined based on the litigation process and the court’s time and expenses incurred.

## 14. Court Fee for an Execution of a Judgment

When an application for the execution of a judgment is brought after the decision is rendered, court fee will be paid as set forth below:

A) Birr 300 (Three Hundred) shall be paid, if the decided amount is between zero and Birr 100,000 (One Hundred Thousand);

B) Birr 500 (Five Hundred) shall be paid, if the judgment is between Birr 100,001 (One Hundred Thousand One) and birr 200,000 (Two Hundred Thousand);

C) Birr 1,000 (One Thousand) shall be paid, if the judgment is between Birr 200,001 (Two Hundred Thousand One) and Birr 500,000 (Five Hundred Thousand);

D) Birr 1,500 (One Thousand Five Hundred) shall be paid, if the judgment is between birr 500,001 (Five Hundred Thousand One) and birr 1,000,000 (One Million);

E) Birr 2,000 (Two Thousand) shall be paid, if the judgment is between Birr 1,000,001 (One Million One) and birr 10,000,000 (Ten Million);

F) Birr 3,000 (Three Thousand) shall be paid, if the judgment is more than Birr 10,000,001 (Ten Million and One);

ሰ) በፍርድ አፋጻጸም ወቅት የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታ አቅራቢው ፍርዱ ሊፈጸምብኝ አይገባም የሚለው ንብረት ወይንም ገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፤

ሸ) የፍርድ አፈጻጸሙ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ጉዳይን የተመለከተ ከሆነ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

G) A person who claims an interest or rights on the properties seized or attached during the execution of judgment shall pay Birr 1,000 (One Thousand) without taking into account the monetary value of the property;

H) Birr 500 (Five Hundred) shall be paid if the Execution of the judgment is for a case that cannot be determined in monetary value.

**፲፭. <u>በግልግል ዳኝነት እና በሌሎች ተቋማት የተሰጠ ውሳኔን ለማስፈጸም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ</u>**

በግልግል ዳኝነት እና በሌሎች የዳኝነት ስልጣን በተሰጣቸው ተቋማት ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ ለማስፈጸም የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፬ ሥር በተደነገገዉ አግባብ ይፈጸማል፡፡

**15. <u>Court Fees paid for the Enforcement of Arbitral Awards and Decisions of other Institutions</u>**

When an application for the execution of an arbitral award issued by arbitrators and Decisions rendered by other institutions with quasi-judicial power is brought to the Court, the Court Fee shall be paid in accordance with Article 14 of this Regulation.

**፲፮. <u>በውጪ አገር የተሰጠን ፍርድ ለማስፈጸም ስለሚከፍል የዳኝነት ከፍያ</u>**

በሕግ አግባብ በውጪ አገር የተሰጠን ፍርድ በፌደራል ፍርድ ቤት ለማስፈጸም የሚያስችል የሕግ ድጋፍ ኖሮት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲፬ በተመለከተው አግባብ ይፈጸማል።

**16. <u>Court Fee for the Execution of Foreign Judgment</u>**

When an application for the execution of a judgment given abroad is brought to be executed in Federal Courts and it has legal bases for its enforcement, the Court Fee shall be paid in accordance with Article 14 of this Regulation.

**፲፯. <u>ለይግባኝ ክርክር ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ</u>**

ይግባኝን በተመለከተ የሚከፈለው ዳኝነት ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡-

፩/ የሥር ፍርድ ቤት በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ላይ ተመስርቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ሳይገባ መዝገቡን የዘጋው ከሆነ በዚህ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድቤት ሲያቀርብ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ዳኝነት ይከፍላል፤

፪/ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲቀርብ በሥር ፍርድቤት ለዳኝነት የተከፈለው ገንዘብ ግማሹን ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል ይደረጋል፤

**17. <u>Court Fee for Appeal</u>**

In case of an Appeal, the Court Fee to be paid according to the following:

1/ When the lower court dismisses the case without entering into the merit of it because of a preliminary objection or any other reasons, the aggrieved party who applies for the Appellate Court shall pay Birr 500 (Five Hundred) as a Court Fee regardless of the Monetary value of the dispute;

2/ When an Appeal is lodged against the decision of the lower Court to the appellate Court, half of the Amount paid at lower Court shall be paid;

፫/ የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነት ከተጠየቀበት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ከፊሉን ወይንም የተወሰነውን ባለመቀበል በከፊሉ ላይ ውሳኔ ከሰጠና ይህንኑ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ከቀረበ ይግባኝ ባዩ ሳይወሰንልኝ ቀርቷል በሚለው ላይ ብቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ በተመለከተው መሰረት ተሰልቶ የዳኝነት ክፍያውን እንዲከፍል ይደረጋል፤

፬/ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ረቺ የሆነ ወገን ውሳኔው የሥነ-ሥርዓት ጉደለት አለበት ወይንም በትክክለኛው ጭብጥ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ አይደለም በማለት መስቀለኛ ይግባኝ ወይንም መስቀለኛ መቃወሚያ የሚያቀርብ ወገን ብር ፩ሺ (አንድ ሺህ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፍላል፤

፭/ መስቀለኛ ይግባኙ ወይንም መስቀለኛ መቃወሚያው የቀረበው በከፊል ውድቅ የተደረገን የውሳኔ ክፍል ከሆነ የዳኝነት ክፍያው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ላይ በተመለከተው አግባብ ተሰልቶ ይከፈላል፤

፮/ ግምቱ በገንዘብ የማይተመን ክስ፣ በአንቀጽ ፲፩ መሰረት በአስተዳደር አካላት የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ ወይንም በቀጥታ አቤቱታ ለሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም ለሚቀርብ ይግባኝ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው ክፍያ ግማሹ የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፤

፯/ ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከዋናው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት በሚችል የትዕዛዝ ይግባኝ ላይ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፤

፰/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውክልና ሥልጣኑ በቀጥታም ሆነ በይግባኝ የሚያያቸው ጉዳዮች ላይ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፪ሺ፲፫ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) መሰረት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲቀርብ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ከ (፩) እስከ (፭) እና (፯) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

3/ When the lower Court decides not to accept all the relief sought but only part of it and the aggrieved party lodges an appeal against the same, the court fee shall be calculated and paid pursuant to Sub Article (2) of this Article only for the amount for which the appellant is aggrieved;

4/ When a winning party in the decision of the lower court brings cross-appeal or cross-objection, claiming that the decision is procedurally flawed or not based on the correct issue, shall pay a Court Fee of Birr 1,000 (One Thousand);

5/ If the cross-appeal or cross objection is for a partially dismissed decision, the Court Fee shall be calculated and paid in accordance with Sub Articles (2) and (3) of this Article;

6/ In the case of non-monetary claims, and when an Appeal or direct application is lodged against the decision rendered by the administrative institution, in accordance with Article 11 of this Regulation, half of the Court Fee paid at the lower Court shall be paid for the Appeal;

7/ Birr 500 (Five Hundred) of Court Fee shall be paid in case an Appeal is lodged against appealable orders for interim service before the main judgment is given;

8/ When an appeal is lodged against a decision rendered by the State Supreme Court on Federal matters in its First-Instance or Appellate Jurisdiction to the Federal Supreme Court, pursuant to Article 9, Sub Article (3) and (4) of Proclamation No. 1234/2021, Sub-Articles (1-5) and Sub Article (7) of this Article shall apply as appropriate;

፱/ በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያ ጉዳዩ ለፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ሊከፈል ይገባ የነበረው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ይከፈላል፤

፲/ በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያው ጉዳዩ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ሊከፈል ይገባ የነበረው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ይከፈላል፤

፲፩/ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ በቀጥታ ለሰበር ችሎት ከቀረበ የዳኝነት ክፍያው በጉዳዩ የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ላይ መሰረት የዳኝነት ክፍያ ይከፈላል፡፡

## ፲፰. <u>በሰበር ለሚታይ ጉዳይ ስለሚከፈል ዳኝነት ክፍያ</u>

፩/ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታውም የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ ለዚህ ፍ/ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ፩/፬ኛ (እሩብ) ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡

፪/ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታውም የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ ለዚህ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ፩/፬ኛ (እሩብ) ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡

፫/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፩ ላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ለመጨረሻው ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡

፬/ ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከዋናው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት በሚችል ትዕዛዝ ላይ ተመስርቶ ከይግባኝ በኋላ የሰበር አቤቱታ ሲቀርብ ለይግባኝ ሰሚው የመጨረሻ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ ለሰበር ችሎት ዳኝነት ይከፈላል፡፡

9/ When an appeal is lodged in the Federal High Court against an arbitral award, the court fee to be paid shall be half of the court fee that would have been paid if the case had been brought to the Federal First Instance Court;

10/ When an appeal is lodged in the Federal Supreme Court against an arbitral award, the court fee to be paid shall be half of the court fee that would have been paid if the case had been brought to the Federal High Court;

11/ If an arbitral award is directly appealed to the Cassation Bench, the Court Fee shall be paid based on the amount of Money involved in the case, in accordance with Article 18, Sub Article (1) or (2) of this Regulation.

## 18. <u>Court Fee for Cases to be Entertained at the Cassation Bench</u>

1/ If the application brought for the cassation is on monetary claims cases and is against the decision of the Federal High Court, 1/4 (One quarter) of the Court Fee paid to this Court shall be paid for the Cassation Bench Judicial Service.

2/ If the application brought for the Cassation is on cases of Monetary claims and is against the decision of the Federal Supreme Court, 1/4 (One quarter) of the court fee paid to this Court shall be paid for the Cassation Bench Judicial Service.

3/ When an application is brought for cassation based on matters addressed under Article 11 of this Regulation, half of the court fee paid to the last court shall be paid to the Cassation Bench Judicial Service.

4/ On orders of interim service, when a post-appeal application is filed in the Cassation Bench regarding an order appealable before the original judgment, half of the court fee paid to the appellate court of the last resort shall be paid to the Cassation Bench.

፭/ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፪ሺ፲፫ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ)፣ (መ) እና (ሠ) በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ለሰበር ችሎት ሲቀርቡ ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተመለከተው የዳኝነት ክፍያ እንደየአግባብበቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፮/ በአስተዳደር አካል የአስተዳደር ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሰበር ችሎት በቀጥታ በሚቀርብበት ጊዜ ብር ፩ሺ፭፻ (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) ይከፍላል፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች</u>**

**፲፱. <u>በዳኝነት ክፍያ መጠን ላይ ስለሚፈጠር አለመግባባት</u>**

፩/ የዳኝነት ክፍያን የሚያስፈጽም የፍርድ ቤቱ ባለሙያ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተከትሎ ክፍያውን ማስፈጸም አለበት፡፡

፪/ በፍርድ ቤት ባለሙያና በባለጉዳዩ መካከል ከዳኝነት ክፍያ ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳዩ ኃላፊነት ለተሰጠዉ ሬጅስትራር ለውሳኔ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ኃላፊነት የተሰጠዉ ሬጅስትራር የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ይህንን ደንብ፣ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን እና ሌሎችንም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት በማድረግ ተለዋጭ ቀጠሮ ሳይሰጥ በገለልተኛነት ስሜት በዕለቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬/ በዳኝነት አከፋፈል ረገድ ኃላፊነት የተሰው ሬጅስትራር የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ባለጉዳዩ አቤቱታውን ጉዳዩን ለሚያየው ችሎት ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ ከፍርድ በኋላ ወደ ይግባኝ ሰሚ ወይም ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ አግባብ የሆነበትን ምክንያት በመጥቀስ ለይግባኝ ሰሚው ወይንም ለሰበር ችሎት ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር ለችሎቱ ማቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ችሎትም የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ በማነስ ወይም በመብለጥ ከሆነ ተስተካክሎ እንዲከፈል ወይም በትርፍነት የተከፈለው እንዲመለስ ትዕዛዝ መሰጠት ይችላል፡፡

5/ When an application for Cassation is filed against the final decision of a State Supreme Court or the Addis Ababa and Dire Dawa Municipal Courts, pursuant to Article 10, Sub Article 1 (a), (d), and (e) of Proclamation No. 1234/2021, the court fee under Sub-Articles (1)-(4) of this Article shall apply as appropriate.

6/ Birr 1,500 (One Thousand Five Hundred) shall be paid when a case of an administrative decision rendered by an administrative agency is filed directly in the Cassation Bench.

**<u>SECTION THREE</u>**

**<u>VARIOUS ISSUES</u>**

**19. <u>Disputes as to the Amount of Court Fee</u>**

1/ An expert responsible for enforcing the court fee shall execute it as per the provisions of the Regulation.

2/ in case of a dispute between the Court officer and the applicant concerning the court fee, the matter should be referred to the authorized registrar for a decision.

3/ After hearing the arguments of both parties, the authorized registrar shall make an impartial decision in accordance with this Regulation, the Code of Civil Procedure, and other relevant laws on the same day, without adjournment.

4/ If the applicant is aggrieved by the registrar's decision on matters related to the payment of the court fee, he shall submit an application to the Bench hearing the case.

5/ Without prejudice to Sub Article (4) of this Article, when the case is brought before the Appellate or Cassation Bench after the judgment, the court fee paid at the trial court may be submitted along with the complaint to the Appellate or Cassation Bench. The Bench to which the complaint has been submitted may investigate the matter, and if the court fee paid at the lower court is deemed too low or too high, the Bench may issue an order for adjustment, payment, or the return of the excess amount paid.

## ፳. <u>ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ</u>

ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው አግባብ ለከፋዩ ሊመለስ ይችላል፤

፩/ ከሳሽ የሆነው ወገን የዳኝነት ክፍያውን ፈጽሞ መዝገቡ ቀጠሮ ከመያዙ በፊት ወይም ቀጠሮ እንደተሰጠው መጥሪያው ወጪ ከመሆኑ በፊት ክሱን ለማቋረጥ ቢወስን ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ላይ ፭ በመቶ (አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ይመለስለታል፡፡

፪/ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ከሳሹ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መነሻ ምክንያት የለውም ወይም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መዝገቡን ቢዘጋ ከተከፈለው ዳኝነት ላይ ፲ በመቶ (አሥር በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ለከሳሹ ይመለስለታል፡፡

፫/ ከክስ መሰማት በፊት ክስ ቢቋረጥ ከተከፈለው ዳኝነት ፲፭ በመቶ (አሥራ አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፬/ ዳኝነት ተከፍሎ የተከፈተ መዝገብ ጉዳዩ በዳኛ አማካኝነት ለፍርድ ቤት መር አስማሚ ተመርቶ፤ ጉዳዩ በአስማሚ በኩል እልባት ካገኘ ከሳሹ ወይም ይግባኝ ባዩ ለዳኝነት የከፈለው ገንዘብ በፍርድ ቤት መር አስማሚነት መመሪያ ላይ በተቀመጠው አግባብ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፭/ ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ከክስ መስማት በፊት በስምምነት ወይም በእርቅ ቢጨርሱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ በተመለከተው መሰረት ከተከፈለው ዳኝነት ላይ ተቀንሶ ለከሳሹ ይመለሳል፡፡ ተከሳሹም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቦ ከሆነ በዚሁ አግባብ ይፈጸማል፡፡

፮/ ከሳሹ ከክስ መስማት በኋላ ክሱን ቢያነሳ የዳኝነት ክፍያው ሙሉ በሙሉ አይመለስም፡፡

## 20. <u>Refunding of Court Fee</u>

Court Fee paid may be refunded to the payer in the following manner;

1/ If the plaintiff decides to withdraw the case before an adjournment is given or before the summons is issued, 5% (Five Percent) of the court fee paid shall be deducted, and the remaining balance shall be refunded to the plaintiff.

2/ If the Court to which the suit is brought dismisses the case on the grounds that the plaintiff has no reason to bring the suit or the Court lacks jurisdiction to adjudicate the matter, 10% (Ten Percent) of the court fee paid shall be deducted, and the remaining balance shall be refunded to the plaintiff.

3/ If the case is interrupted before Trial, 15% (Fifteen Percent) of the Court Fee paid shall be deducted, and the remaining balance shall be refunded to the plaintiff.

4/ If, after the required court fee is paid and the case is opened, the case is referred to a Court-annexed mediator by a judge and is settled through mediation, the court fee paid by the plaintiff or appellant shall be refunded in accordance with the Court-annexed mediation Directive.

5/ If the disputing parties settle their dispute through conciliation before the hearing of the suit at trial, the amount referred to in Sub Article (2) of this Article shall be deducted from the court fee paid, and the remaining balance shall be refunded to the plaintiff. If the defendant has instituted a counter-claim, the same process shall apply.

6/ The total court fee shall not be refunded if the plaintiff withdraws the suit after the trial has begun.

## ፳፩. የዳኝነት ክፍያ የማይከፈልባቸው ጉዳዮች

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ክፍያ አይከፈልም፡-

፩/ የቀለብ ክፍያና የልጅ አስተዳደግን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ፤

፪/ በሴቶች፣ በሕጻናት፣ በአረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞችን እንዲሁም ሌሎች ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ የሚቀርብ የሕዝብ ጥቅምን ለማስከበር ወይም አካልን ነጻ ለማውጣት እና ሌሎች የወል ሰብዓዊ መብታቻቸዉን ለማስከበር በሲቪል ማኅበራት አማካይነት የሚቀርብ ክስ፤

፫/ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤን በሚመለከት የሚቀርቡ ጉዳዮችን፤

፬/ በሕግ አግባብ በድሃ ደንብ እንዲከራከር በፍርድ ቤት የተወሰነለት ሰው፤

፭/ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክርክር፤

፮/ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት አንድ ሰራተኛ በግሉ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስለት ለሚያቀርበዉ አቤቱታ።

## 21. Matters Exempted from Court Fee

Without prejudice to the provisions of other laws, no court fee shall be payable in the following cases:

1/ Applications regarding alimony and child custody;

2/ Suits for the enforcement of the collective and basic human rights of women, children, elderly persons, persons with disabilities, matters related to vulnerable groups of the society, public interest suits and suits of Habeas Corpus brought by Civil society organizations;

3/ Cases related to Environmental protection;

4/ A person allowed to bring the Suit as a Pauper in accordance with the law;

5/ Criminal Cases;

6/ An application submitted by an individual Employee for judicial review of a decision rendered by an Administrative Agency.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፪. መመሪያ ስለማውጣት**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**፳፫. የተሻሩ ሕጎች**

፩/ ስለዳኝነት ክፍያ የወጣው ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፩፻፸፯/፩ሺ፱፻፶፪ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህንን ደንብ የሚጻረሩ ማናቸውም አሰራሮች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

**፳፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯**

**ታገሰ ጫፎ**
**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ**

## SECTION FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**22. Issuing a Directive**

The Federal Supreme Court may, when deemed necessary, issue a Directive for the implementation of this Regulation.

**23. Repealed Laws**

1/ The Court Fee rule under legal notice No. 177/1952 is hereby repealed by this Regulation.

2/ Any practice inconsistent with this Regulation is hereby repealed.

**24. Effective date of the Regulation**

This Regulation shall be effective from the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa On 7th May, 2025**

**TAGESSE CHAFO**
**SPEAKER OF THE HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES**